# ይድረስ ለአባ ጳውሎስ !

ወለላዬ ከስዊድን welelaye2@yahoo.com

**እኔን የምትመስሉ ሁኑ ወንድሞች ሆይ፣**
**ምሳሌ ሆናችሁ ሂዱ በአደባባይ።**
**የሚመላለሱት ለክርስቶስ መስቀል፣**
**እስከዛሬ ድረስ ጠላቶች ሆነዋል።**
**አሁንም በማልቀስ እናገረዋለሁ፣**
**ይሄ ሁሉ ከንቱ መሆኑን አውቃለሁ፣**
**ምድራዊነት ይዞ ጸያፍ ነውራቸው፣**
**መጨረሻው ጥፋት ከንቱ ነው ክብራቸው፣**
**ሆዳቸው ይሆናል የነሱ አምላካቸው።**
*ፊሊጵዮስዮስ፣ ም .3፣ ቁ .17-20*

ባልችልም ደፍሬ አባቴ ለማለት፣
እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ አዛውንት፣
ተገቢ የሆነ አክብሮት ሳይቀንስ፣
ይሄ ደብዳቤዬ ይድረስ ለአባ ጳውሎስ።
ሀገር ችግር ስቃይ ደጋግሞ ሲንጣት
በጨካኝ መሪዎች ልጆችዋ ሲያልቁባት፣
ያልሰሙ ያላዩ መስለው በመደበቅ፣
ዙፋን ላይ ተቀምጠው ተሸሞንሙነው በወርቅ
ሕግን ሳይጠብቁ ሥርዓት ሲያፈርሱ፣
አስራ ስምንት ዓመት ከረሙ ሲያምሱ።
ይሄ ሳያንስዎ ንጹኅ መነኩሴ፣
ታዋቂ አባታችን ፍቃደሥላሴ፣
እንደወንጀለኛ የጦር ሜዳ ቅጣት፣
ተደብድበው ሞቱ ፊትዎ በጥይት።
ምርጫን አስመልክቶ ያ ሁሉ ደም ሲፈስ፣
ሆነው ቂብ ብለው ያገሪቷ ጳጳስ፣
አጥፊን ሳያወግዙ ወይም ሳይገዝቱ፣
ወላጅ ሳያጽናኑ ሙታንን ሳይፈቱ፣
እርስዎ እንዳልቆሙ ከገዳይ በማበር፣
አልቻሉም ሊያሳዩ ተቃውመው በተግባር።
ጋምቤላ በደኖ ህዝቡ ሲጨፈጨፍ፣
አሶሳ አዲሳ'ባ እንደቅጠል ሲረግፍ፣
ተማሪ እንቢ ብሎ ተቃውሞ ሲያሰማ፣
በአጋዚ ጥይት ሲገደል ሲደማ፣
እናትና ልጅን ደራርበው ሲጥሉ፣
ተቀምጠው ከርመዋል ጭጭ ዝም እንዳሉ።
ከጣሊያን በከፋ በዚያ እልቂት ወራት፣
መቃወም ባይችሉም ቢፈሩም እስራት፣
እንደምን ደፈሩ ግብር አብሮ መብላት።
ከዛም አልፈው ተርፈው አሁን ደግሞ ዛሬ፣
ጭራሽ የሚያስፈራ ሰማሁ ክፉ ወሬ።
ተሰብስቦ አብሮ አንድ ላይ ሲኖዶስ፣
ባደረጉት በደል እርስዎን በመውቀስ፣
ይብቃዎት እንግዲህ ይኑሩ በፀሎት፣
ያስተዳደር ሥራ ሌሎች ይሥሩልዎት፣
ብሎ ቢያኖርዎ ሁሉን አመቻችቶ፣
አሜን እንደማለት የርስዎ ቀረርቶ፣
ኧረ ምን ይባላል አልገባኝም ከቶ።
ቶሎ እንደመቀበል ይሄን በምስጋና፣
ሕገ ደንብ ሽረው አፍርሰው ቀኖና፣
አሻፈረኝ እንቢ ሥልጣኔን አለቅም፣
ብለው ማለትዎ ተታለው በጥቅም፣
መጨረሻው ጥፋት ከንቱ ነው ክብራቸው፣
ሆዳቸው ይሆናል የነሱ አምላካቸው፣
እንዲል መጽሐፉ ያስከትላል ውርደት፣
ብጹዕ አባታቸው በቶሎ አስቡበት።
እንደውም እንደውም ጨዋ ናቸው ደጎች፣
ፍርዱን የበየኑት እነዚህ አባቶች።
በያዙት ማዕረግ በጨበጡት ሥልጣን
ይችላሉ እሙኑኝ ለመጉዳት እርስዎን።
ወዳጅ ነው የሚሉት መንግሥትም እራሱ፣
አይቀርም መፍረዱ ሆኖ ወደነሱ።
አሁን የፈጸሙት ከፋትና ደባ፣
ማስፈራራትና የአባቶች ድብደባ፣
እንደ አባጨጓሬ ነገ በመኮስኮስ፣
ያሰቃይዎታል ይወቁበት ጳውሎስ።
ፍርዱን ይቀበሉ ስለዚህ በቶሎ፣
ወደ ገዳም ይግቡ ደርበው ደበሎ።
መሬት ላይ ይተኙ በቃ ማቅ ይልበሱ፣
ወደ ፈጣሪዎ ፊትዎን ይመልሱ።
ብዕር ብጨብጥም ባነጥፍ ወረቀት፣
በፈጣሪ ፈቃድ ነውና የጻፍኩት፣
ይከፋል ነገሩ አይቆዩ እስከጥቅምት።
ሊረዳዎት ቢችል ሐቅን ለማስታወስ፣
ይሄ ደብዳቤዬ በአድራሻዎ ይድረስ!

ወለላዬ ከስዊድን welelaye2@yahoo.com
ሐምሌ 14 ቀን 2001 ዓ.ም. July 21, 2009